በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

ሰብዕ *- (መነባንብ)*

ለሰው ሰውነቱ - ከአፈር መስማማቱ፤
የሸክላ ብርታቱ - እሳት ነው ጉልበቱ፤
ውሃም ደም ግባቱ - ነበር መድሃኒቱ፤
ታዲያ ምን ያደርጋል...
ከነፋስ ተዋዶ - ዕድሜውን ጠቅልሎ - ይሮጣል ለሞቱ፡፡
ሰው ለሰውነቱ
ከእሳት ነው ሥሪቱ፤
ያገኘውን ሁሉ - ለብልቦ አየበላ፤
በደሉ በዛና - በምድር ሁሉ ሞላ፡፡
ምድርን ሊያጠፋት - እግዚአብሔር ቢገለጥ - በሰው ተቆጥቶ፤
ከእልፍ አዕላፋት ሰው - ኖኅን ተመልክቶ፤
መቶ ሃያ ዓመታት - ከቁጣው ዘገየ - ለአንዱ ኖኅ ራርቶ፡፡
ሰው በሰውነቱ - እሳት በርትቶበት
መቶ ሃያ ዓመታት...
በሃጢኣት ይባላል - ለሃጢኣት ይበላል፤
ኖኅ ግን በጽናቱ - መርከቡን ይሠራል፡፡
ውሃ ለጥፋቱ - ከእሳት ይበረታል፤
የታላቁን ቀላይ - ምንጮች ያፈነዳል፤
የሰማዩ መስኮት - ርኩሰት ያፀዳል፤
ኖኅና መርከቡን - ከምድር ለይቶ - ከፍ - ከፍ - ያደርጋል፡፡
ኖኅም ከእግዚአብሔር ጋር - ቃል ኪዳን ገባና፤
ሰማይ ተጋረደ - በቀስተ ደመና፡፡
ታዲያ... ታዲያ በዚህ ዘመን - ዘመን በዘመን ላይ - አድሮ እየዘመነ፤
በዚህ ጠባብ ትውልድ - ያ የኖኅ ቃል ኪዳን - ቀለም ብቻ ሆነ፡፡

በአባቱ ተጋድሎ - ልጁ እያፈረ፤
ማንነቱን ገድሎ - ታሪኩን ቀበረ፡፡
ከሀሠት ተጋብቶ - ከተኩላ ጋር ዋለ፤
የወርቅ ቀለሙን - ብራናውን ፍቆ - ተረት ተረት አለ፡፡
ከባህር ዳር ሆነው - ጸንቶ ማዕበሉ፤
ቀስተ ደመናውን - አሻግረው እያዩ - የላም በረት አሉ፡፡ የላም በረት!
ከምዕራቡ ዓለም - በሚነፍሰው ነፋስ - ለቁሩ ለብርዱ፤
ከዚያች ከኖኅ መርከብ - ፍልጥ እየፈለጡ፤
ለተረት ማድመቂያ - እሳት አነደዱ፡፡

እሳት አነደዱ - ይነዳል እሳቱ፤
ጊዜ እየቆጠረ - ይነጉዳል ሌሊቱ፡፡
የጠቆረው ሰማይ - ደመና እያዘለ፤
መብረቅ ነጎድጓዱ - ባህሩን ከፈለ፡፡
እያስገመገመ ዝናቡ ወረደ፤
ማዕበሉ አይሎ - አሸዋው ተናደ፡፡
ባላሰብናት ሰዓት - ድንገት ተገለጠች፤
ሞት በላያችን ላይ - ውቅያኖስን ሆነች፡፡
ያች የኖኅ መርከብ ግን - ከፍ - ከፍ - እያለች፤
አራራት ላይ ቆመች፡፡
ዶሮ ካልተሰማ - በሌሊት ጩኸቱ፤
ድሮም ለእሳቱ - ውሃ ነው ቅጣቱ፡፡
የዶሮውን ጩኸት - በሌሊቱ የሰሙ፤
በጴጥሮስ ንስሃ - ዳግም እየቆሙ፤
ሥሉስ ቅዱስ ብለው - እያመሰገኑ፤
ሳይወጡ ሳይወርዱ - በመርከቧ ጸኑ፡፡
ለነገሥታት ንጉሥ - ለአማልክት አምላክ - ለጌቶችም ጌታ - ቅኔ እየተቀኙ፤
የመርከቧን ምሥጢር - እያመሰጠሩ፤
በዱር በበረሃ - በዋሻ እያደሩ፤
ለክብር ለትሩፋት - በወንጌል የኖሩ፤
በማርያም መቀነት - በቀስተ ደመናው - ለምህረት ተጠሩ፡፡
የአባቶችን ድንበር - ተግተው የጠበቁ፤
ቀድመው የተጠሩ - የተጠሩት ሁሉ - ከብረው የጸደቁ፤
ሃሌ ሉያ እያሉ... ሃሌ ሉያ እያሉ - እያሸበሸቡ፤
በዚያች በኖኅ መርከብ - ወደማያልፈው ክብር - ወደእቅፉ ገቡ፡፡
የኖኅ ቃል ኪዳኑ - ዛሬም የጸናባት፤
መብረቅ ነጎድጓዱ - ያላነዋወጣት፤
የኢየሱስ ክርስቶስ - ሥጋውና ደሙ የሚፈተትባት፤
የመንግሥተ ሰማይ - የገነት በር ናት...
ያች የኖኅ መርከብ - ቤተ-ክርስቲያን ናት !!

ቤተ-ክርስቲያን...
በዕውቀት አጎልምሳ - ጥበብ አጎናጽፋ - ኑ! ልጆቼ ብላ - ሁሌ የምትጣራ፤
የኖኅ መርከብ ተምሳሌት - የመልካም ሰው መልካም ሥፍራ፡፡
ቤተ-ክርስቲያን...
እጅግ ጥልቅ የሆነች - የማትመረመር፤
ቤተ-ክርስቲያን ናት የጥበባት ባሕር፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር